OFFICE OF THE COUNTY EXECUTIVE

Marc Elrich
County Executive

ቀን፡ ህዳር 1, 2020

ውድ ጓደኞቼ

የፖሊስ የኃይል አጠቃቀምን ያካተተ አገራዊ እና አካባቢያዊ ክስተቶች በአገሪቱ እና በዚህ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ በፖሊስ መዋቅር እና የገንዘብ ድጋፍ ላይ ትኩረትን ስበዋል ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ (ኤም.ሲ.ፒ.ዲ.) ስራዎችን እና ኃላፊ ነቶችን ለመገምገም ስፈልግ የተወሰነ ጊዜ ሆኖኛል::እናም ስራውን የጀመርኩት ባለፈው ዓመት ነው :: የማህበረሰብ ተሳትፎን ባ ካተተ ሂደት አዲስ የፖሊስ አዛዥ ቀጥረናል ።በሌሎች የፖሊስ መኮንኖች ከመጠን በላይ የሆነ ኃይል መደረጉን ሲመለከቱ ፖሊሶ ች ጣልቃ እንዲገቡ የሚያስገድድ ፖሊሲ "ጣልቃ የመግባትን ግዴታ" በተመለከተ ከፖሊስ ማኔጅመንትና ከዩኒየን ጋር ስምምነ ት ላይ ደርሰናል። እኛ የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ ስራዎችን የሚቆጣጠር እና የፖሊስን ሥራ በሲቪል ቁጥጥር ስር ለማድረግ በ ሚደረገው ጥረት አካል እንዲሆን እና የፖሊስ መምሪያ ማህበራዊ ፍትህ ጥረቶችን ለመምራት የሚደረገው ጥረት አካል የሆነ ሲ ቪል ረዳት የፖሊስ አዛዥ ፈጥረናል።ከቤት አልባነት ጋር የተያያዙ የወንጀል ቅጣቶችን ማለዘብ ወይም ማስወገድ ላይ የ ሚሰራ አንድ ቡድን ሰብስቤ ነበር ።አሁን ድርጊታችንን ለመምራት የሚረዳ ሪፖርታቸውን አግኝተናል። በተጨማሪም ድህነ ትን ለማውረድ የኤም.ሲ.ፒ.ዲ ገለልተኛ እና የዘር አድልኦ ኦዲት ለማድረግ አማካሪ አሰማርተናል። እዚህ ያልተካተቱ ግልጽ ያ ልሆኑ ፣ ሥርዓታዊ እና/ወይም የዘር አድልዎ ካሉ እነሱን እንዴት መፍታት እንደሚቻል ምክሮችን በደስታ እንቀበላለን እና በጥብቅ እንመረምራለን ።

እኛ የካውንቲ መንግስት ውስጥ ይህንን ሥራ ለብቻ መስራት አንችልም እናም በካውንቲው ውስጥ የፖሊስ ሥራን እንድናሻ ሽል እና የህዝቡን ደህንነት እንደገና እንድናየው የማህበረሰብ አጋሮቻችን ያስፈልጉናል።ካውንቲውን የበለጠ ፍትሃዊ ለማድረግ የሕዝባዊ ደህንነት ጥረቶቻችንን በጥልቀት ለማወያየት እና ለመገምገም ካውንቲውን በማህበረሰብ ፍላጎቶች ላይ እንዲሁም የ ወጪዎችን ቅደመ ተከተል በምናመጣጠንበት ሁኔታ ላይ ተመስርተን ለህዝቦች ደህንነት እንደገና በማህበረሰባችን ውስጥ የበለ ጠ ኢንቬስት ለማድረግ እንዲመክሩን "እንደገና የህዝብ ደህንነት የማገናዘብ ግብረ ኃይል" አቋቁሚያለሁ ።የፖሊስ መኮንኖች ከፖሊስ ሥራ ጋር ተዛማጅነት ለሌላቸው ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት ከፍተኛ ጊዜያቸውን እንደሚያጠፉ ከፖሊስ ኃላፊው እና ከሌሎች የፖሊስ መምሪያዎቻችን ሰምተናል። የፖሊስ ሥራን እንዴት መቀየር እንዳለብን ማወቅ አለብን ፤ ስለዚህ ፖሊ ሶች ማድረግ ያለባቸውን ነገሮች እንዲያደርጉ እንጂ ማድረግ የሌለባቸውን ነገሮች እንዳያደርጉ ።

ግብረ ኃይሉ 46 የማህበረሰብ ተወካዮችን ያካትታል ፡ ሆኖም ግን ፣ ከብዙ የማህበረሰብ አባላት መስማት እፈልጋለሁ እና በዚ ህ የማህበረሰብ ግብዓት ዳሰሳ ላይ እንዲሳተፉ እጋብዛለሁ። የዳሰሳ ጥናቱ አሁን ይገኛል እስከ ህዳር (ኖቬምበር) 14 ቀን 2020 ክፍት ሆኖ ይቆያል። ምላሾችዎን ሰብስበን መረጃውን ከመረመርን በኋላ ውጤቱን የምንወያይበት የማህበረሰብ መድረክ እናደርጋለን። በዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች ላይ ለምናባዊ የማህበረሰብ ውይይት እባክዎ ታህሳስ (ዲሴምበር) 3 ቀን 2020 ከእ ኔ ጋር ለመገናኘት ያቅዱ ።
ስለ ጊዜዎ እና ስለግብአትዎ አመሰግናለሁ። ሀሳቦችዎን ለማንበብ እና በታህሳስ (ዲሴምበር) ወር ውስጥ ላዮት እጓጓለሁ ።

ከሰላምታ ጋር

ማርክ ኤልሪች

101 Monroe Street • Rockville, Maryland 20850
240-777-2500 • 240-777-2544 TTY • 240-777-2518 FAX
www.montgomerycountymd.gov